አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

ቁጥር 26, መስከረም 2016 ዓ.ም Issue No. 26, September 2023

# አዋሽ ዜና መጽሔት

# Awash Newsletter

በብራንዲንግና ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የሚታተም
Published by: Branding & Communication Directorate

አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like The River



# Branch
## Banking Made Easy

- Bole Getu Commercial Center
- Bisrate Gebriel
- Adama

8980

www.awashbank.com

Connect with us

ዋና አዘጋጅ: ተሾመ ዋቅጅራ

ረዳት አዘጋጆች: ሰላም ተክለጽዮን
ድሪባ መገርሳ
ጋዲሳ አስፋው
ሲሳይ ነዳ
ዲናኦል ዱጋሳ
ጫልቺሳ ገመቹ

ፎቶግራፍ: ዳንኤል ምትኩ

EDITOR-IN-CHIEF: Teshome Wakjira
ASSISTANT EDITORS: Selam Tekletsion
Deriba Megerssa
Gadisa Asfaw
Sisay Neda
Dinaol Dugasa
Chalchisa Gemechu

PHOTOGRAPHER: Daniel Mitiku

8980
12638
www.awashbank.com
contactcenter@awashbank.com

# በዚህ እትም

አዋሽ ባንክ የ2022/23 ዓመታዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማ አካሄደ..................1
አዋሽ ባንክ የጥቃቅን አነስተኛና መካከለኛ ንግድ ዘርፍን በመደገፍ ረገድ ላበረከተው አስተዋፅኦ ከግሎባል ኤስኤምኢ ፋይናንስ ዕውቅና አገኘ .......... 4
አዋሽ ባንክ አዲስ የፋይናንስ ቴክኖሎጂ ይፋ አደረገ.................................... 6
አዋሽ ባንክ የስራ ዕድል ፈጠራን የሚያበረታታ የ 'ታታሪዎቹ'/ ቀጠሌወን የሁለተኛ ዙር ፕሮጀክት ይፋ አደረገ........................................................... 8
ባንኩ ማህበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት በተለያዩ ስፍራዎች ትምህርት ቤት እና የህክምና መስጫ ማዕከል አስገነባ...............................10
ቆይታ ......................................................................................12
ምልከታ......................................................................................19

# IN THIS ISSUE

Photo Reel......................................................................................23

አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

# አዋሽ ባንክ የ2022/23 ዓመታዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማ አካሄደ




የስራ አመራር አባላት ጠቅላላ ጉባኤ የመክፈቻ ስነ ሥርዓት

አዋሽ ባንክ እኤአ የ2022/23 የሂሳብ ዓመት የስራ ክንውን ግምገማ እና የ2023/24 የሂሳብ ዓመት ስትራቴጅክ ዕቅድ ላይ ሐምሌ 28 እና 29 ቀን 2015 ዓ.ም በስካይ ላይት ሆቴል ውይይት አካሂዷል።

የአዋሽ ባንክ ዋና ሥራ አሰፈፃሚ አቶ ፀሐይ ሽፈራው ጠቅላላ ጉባኤውን በመክፈቻ ንግግር በከፈቱበት ወቅት እንደገለጹት በበጀት ዓመቱ የነበሩንን ጠንካራ ጎኖችን በማጐልበት፣ የታዩትን ድክመቶች በማሻሻል፣ እ.ኤ.አ. በ2023/24 ባንካችን ሊተገብራቸው ያስቀመጣቸውን ዕቅዶች በተሻለ የሥራ አፈጻጸም ማከናወን በምንችልባቸው ሥልቶች ላይ የጋራ የሆነ አቋም ይዘን በጋራ በሥራ ላይ ማዋል ይገባል ብለዋል።

አክለውም የ2023/24 የሂሣብ ዓመት ዕቅድ በማሳካት ባንካችን በአገር ውስጥ ካሉ የግል ባንኮች የያዘውን የመሪነት ስፍራ ይዞ እንዲቀጥልና በአምስት ዓመት ኮርፖሬት ስትራቴጂ ውስጥ ያስቀመጠውን የቪዥን 2030 ዓላማዎች ለማሳካት ሁሉም አመራር አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

በተጨማሪም አዋሽ ባንክ ከውጭ ሀገር እና ከሀገር ውስጥ ባንኮች የሚጠበቀውን ውድድር አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት ሁላችንም ዝግጁ መሆን ይጠበቅብናል ሲሉ አሳስበዋል።







የጠቅላላ ጉባኤ ተሳታፊዎች በከፊል

በሌላ በኩል የባንኩ የደንበኞች የግንኙነት ማዕከል (Contact Center) ዓለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ Sound Proof፣ የሰራተኞች መዝናኛ፣ ካፍቴሪያ እና የተለያዩ ክፍሎች ያሉት በአዲስ መልክ አገልግሎት እንዲሰጥ መደረጉ በሪፖርቱ ተጠቅሷል።

ለባንኩ ደንበኞች የሚሰጡትን አገልግሎቶች ለማዘመንና ደንበኞች ያለብዙ ውጣ ውረድና ልፋት በአቅራቢያቸው እና በሚያመቻቸው የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት (Service Delivery Channels) እንዲጠቀሙ ለማስቻል የ E-School Manage- ment System ሥራ ላይ የዋለ ሲሆን ደንበኞች በንግድ ቦታዎች በዱቤ አሰራር ክፍያ እንዲፈጽሙ የምያስችላቸዉ የአዋሽ ክሬዲት ካርድ በይፋ መከፈቱም ተገልጿል።

በተመሣሣይ መልኩ በአሁኑ ጊዜ ባንኩ ከውጭ ሀገር ያስገባቸውን ከ1 ሺህ በላይ የኤቲኤም ማሽኖች በተመረጡ ቅርንጫፎች እና የንግድ ማዕከላት መተከላቸው እና የሼልተር ሥራቸዉም መከናወኑ በሪፖርቱ ይፋ ተደርጓል።

በሂሳብ ዓመቱ የባንኩን የተቀማጭ ሂሣብ እና የውጭ ምንዛሪ ግኝት ለማሣደግ በርካታ ሥራዎች በመሰራታቸዉ ከ1.5 ሚሊዮን በላይ አዳዲስ ደንበኞችን ማፍሪት የተቻለ ሲሆን፣ 75 አዳዲስ ቅርንጫፎችን ከፍቶ ለአገልግሎት በማብቃት ከአዳዲስ ደንበኞች ከብር 20 ቢሊዮን በላይ ተቀማጭ ሂሣብ መሰብሰብ መቻሉን ተጠቁሟል።

አዋሽ ባንክ ማህበራዊ ኃላፊነቱን ከመወጣት አኳያ የሥራ ፈጠራ ክህሎት ያላቸውን ወጣቶች ለማበረታታት ታታሪዎቹ/ ቀጠሌወን የተሰኘውን የውድድር መርሃ ግብር ቀርጾ ውድድሩን በማካሄድ አሸናፊ ለሆኑ ተወዳዳሪዎች እንደየ ደረጃቸው ከብር ሁለት መቶ ሺህ እስከ አንድ ሚሊዮን ሽልማት አበርክቷል፡፡ እንዲሁም የባንኩን የፋይናንሻል አፈጻጸም እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 2022 መጨረሻ ላይ የባንኩ ጠቅላላ ተቀማጭ ሂሣብ ኤልሲ ማርጅንን ጨምሮ ብር 173.12 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ ይህም ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ51 በመቶ ዕድገት ያሳየ ሲሆን ካለፉት ዓመታት ዕድገቶች አኳያም ከፍተኛው መሆኑ ተገልጿል።

በሂሳብ ዓመቱ የእቅዳቸውን 100% እና ከዚያ በላይ ላሣኩ 279 የባንኩ ቅርንጫፎች ዕውቅና የተሰጣቸው ሲሆን በተመሣሣይ መልኩ እ.ኤ.አ ዲሴምበር 2022 መጨረሻ ላይ የተሰጣቸውን ዕቅድ ማሣካት ብቻ ሣይሆን እ.ኤ.አ ለሰኔ 2023 መጨረሻ የተቀመጠላቸውን ዕቅድ ያሣኩ 34 ጀግና ቅርንጫፎች የማበረታቻ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

የባንኩን የተቀማጭ ሂሣብ ክንውን በሂሳብ ዓመቱ ያስመዘገበው ዕድገት 13.7 በመቶ ብቻ ሲሆን፣ በግል ባንኮች የተመዘገበው አማካይ ዕድገት ግን 19 በመቶ ሆኗል፡፡ ይህም ዕድገቱን ከሌሎች ባንኮች አንጻር አዝጋሚ መሆኑን ያሣየ መሆኑ ተገልጿል።

የውጭ ምንዛሪ ግኝትን በተመለከተ ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የ25 በመቶ ዕድገት ወይም የ158.3 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ጭማሪ በማሳየት እ.ኤ.አ ዲሴምበር 31, 2022 ላይ 783 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ሆኗል፡፡ ከወጪ ንግድ፣ ከSWIFT እና ከውጭ ምንዛሪ ግዥ የተገኘው የውጭ ምንዛሪ ግኝት 100% ዕቅዱን ማሣካት ችሏል፡፡ ነገር ግን ከውጭ ሀገር ሀዋላ የተገኘው የውጭ ምንዛሪ ከአምናው ተመሣሣይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ46 በመቶ ቅናሽ አሣይቷል፡፡ ምንም እንኳን የጥቁር ገበያው የምንዛሪ ዋጋ መናር ለውጭ ሀገር ሀዋላ ቅናሽ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ቢኖረውም፣ የደንበኞች አገልግሎታችንን በማሻሻል፣ የውጭ ሃገር የሃዋላ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ቁጥር በማብዛት እና የተለያዩ የማበረታቻ ስልቶችን በመጠቀም የሐዋላ የባንኩን ገቢ ማሣደግ እንደሚገባ አቶ ፀሐይ አሳስበዋል።




የላቀ ውጤት ያስመዘገቡ ተሸላሚ ቅርንጫፎች

ባንኩ ለተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች የሰጠው የብድር መጠን ብር 158.2 ቢለዮን የደረሰ ሲሆን ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የ61 በመቶ ዕድገት አሣይቷል፡፡ በተለይ ለወጪ ንግድ (Export Sector) የሰጠው ብድር የ24.6 በመቶ ዕድገት በማሣየት ብር 29.96 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ የባንኩ ጠቅላላ ገቢ ባለፈው ዓመት ተመሣሣይ ወቅት ከነበረበት ብር 9.8 ቢሊዮን የብር 3.8 ቢሊዮን ጭማሪ በማሳየት ብር 13.6 ቢሊዮን ሆኗል፡፡ ይህም ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት አንጻር የ40 በመቶ ዕድገት አሣይቷል፡፡ የባንኩ ጠቅላላ ወጪ ደግሞ የብር 2.9 ቢሊየን ወይም የ55 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ ብር 8.2 ቢሊዮን ሆኗል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የባንኩ ያልተጣራ ትርፍ እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 2022 መጨረሻ ላይ ብር 5.4 ቢሊዮን ሲሆን ይህም ትርፍ ከአምናው ተመሣሣይ ወቅት አኳያ የ21 በመቶ ዕድገት ያስመዘገበ ቢሆንም በዘጠኝ በመቶ ከእቅድ በታች ሆኗል፡፡

በውይይቱ ወቅት እንደተገለፀዉ ባንኩ ደካማ አፈፃፀም ያሳየባቸዉ የተጨማሪ የቁጠባ ሂሣብ መጠን (Additional Savings) ከሌሎች ተወዳዳሪ ባንኮች አንጻር አነስተኛ ሆኖ ተገኝቷል።

ለዚህ ደግሞ ዋነኛው መንስኤ ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት ተቀማጭ ሂሣብ (IFB Deposits) ከሌሎች ባንኮች አንጻር ዝቅተኛ ሆኖ መገኘት ነው።

የመድርኩ ተሳታፊዎች በሰጡት አስተያየት ባንኩ የተወሰኑ ክፍተቶች ቢኖሩበትም እስካሁን ባለዉ አቋም የተሻለ አፈጻፀም እንዳለዉና መሪነቱን ለማስቀጠል ያሉበትን ክፍተቶቹን በመሙላት የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ እንደሚሰሩ በመግለጽ በቀጣይ ጊዜያት አቅማቸዉን በማጠናከር እና በመተባበር ለ2023/24 ሂሣብ ዓመት የተቀመጡ ዕቅዶች መሉ በሙሉ ለማሳካት ከወዲሁ በቁርጠኝነት እንደሚሰሩ ቃል ገብቷል።

በመጨረሻም የጠቅላላ ጉባኤው ተሳታፊዎች ባለአስር ነጥብ የአቋም መግለጫ ያወጡ ሲሆን በመግለጫቸዉም ባንኩ ያለበትን ክፍተት በመሙላት፣አዳዲስ ሃሣቦችንና ቴክኖሎጂዎችን ተግባራዊ በማድረግ፣ የነቃ ተሳትፎ በማድረግ እና የስብሰባውን ውሳኔዎች ተግባራዊ በማድረግ ለባንካቸዉ ያላቸዉን ወገንተኝነትና ተቆርቋሪነት አጠናክረው እንደሚሰሩ ቃል በመግባት ጉባኤው ተጠናቋል።

# አዋሽ ባንክ የጥቃቅን አነስተኛና መካከለኛ ንግድ ዘርፍን በመደገፍ ረገድ ላበረከተው አስተዋፅኦ ከግሎባል ኤስኤምኢ ፋይናንስ ዕውቅና አገኘ




የግሎባል ኤስኤምኢ ፋይናንስ የዕውቅና አቀባበል ስነ ሥርዓት

አዋሽ ባንክ የጥቃቅን አነስተኛና መካከለኛ ንግድ ዘርፍን በመደገፍ ረገድ ላበረከተው አስተዋፅኦ ከግሎባል ኤስኤምኢ እ.ኤ.አ የ2023 ዕውቅና አግኝቷል።

በህንድ ሙምባይ በተካሄደውና ከ700 በላይ ተሳታፊዎች በተገኙበት ግሎባል ኤስኤምኢ ፋይናንስ እ.ኤ.አ የ2023 አዋሽ ባንክ አነስተኛና መካከለኛ ንግድ ዘርፍን በመደገፍ ረገድ ላበረከተው አስተዋፅኦ ለመጀመሪያ ጊዜ ከአፍሪካ ሀገሮች መካከል አለም አቀፍ ዕውቅና ማግኘት ችሏል።

የዓለም አቀፉ የኤስኤምኢ ፋይናንስ ፎረም በዋናነት የአነስተኛ እና መካከለኛ ንግዶች የፋይናንስ አቅርቦትን ለማስፋፋት የሚሰራ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ፎረሙ የፊንቴክ ኩባንያዎችን ማለትም የፋይናንስ እና የቴክኖሎጂ ኩባንያዎችን እና የልማት ፋይናንስ ተቋማትን አንድ ላይ በማሰባሰብ የአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን የስራ ክህሎት ፈጠራን የሚያበረታታ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ፎረሙ ከ240 በላይ አባላትን አፍርቷል።

እ.ኤ.አ. በ 2018 የተጀመረው እና አሁን ስድስተኛ ዓመቱን የያዘው የዓለም አቀፍ ኤስኤምኢ ፎረም አነስተኛና መካከለኛ ንግድ ዘርፍ ወደላቀ ደረጃ በማሳደግ ረገድ ከተለያዩ ተቋማት ጋር በመቀናጀት በርካታ ጥረቶችን ሲያደርግ የቆየ ሲሆን በተለይ ፎረሙ ዘንድሮ ለሽልማት እጩ ካደረገው ይፋዊ ምድቦች ውስጥ በዋናነት፡- የዓመቱ የጥቃቅን አነስተኛና መካከለኛ ንግድ ዘርፍን በፋይናንስ የደገፉ ተቋማትን፣ በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን ተጠቃሚ የሚያደርጉ አዳዲስ ምርቶችን (Products) እና አገልግሎቶችንና ምርቶችን ላበረከቱ ተቋማትን፣ ሴት የስራ ፈጣሪዎችን በማበረታታት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉ እንዲሁም በአረንጓዴ ልማትና ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድ በዓመቱ ተጨባጭ እና ዘላቂነት ያለው ውጤት ማምጣት የቻሉ ተቋማትን በዕውቅና የሽልማት ምድብ ውስጥ ያካተተ ነበር፡፡

አዋሽ ባንክ በ2023 ግሎባል ኤስኤምኢ ፋይናንስ ካስቀመጠው የሽልማት ዝርዝር ውስጥ በመጀመርያው ምድብ ማለትም የጥቃቅን አነስተኛና መካከለኛ ንግድ ዘርፍን ከፍተኛ መዋለ ንዋይ በማፍሰስ ዘርፉን በፋይናንስ በመደገፉ የዓለም አቀፍ ዕውቅናውን መቀዳጀት ችሏል፡፡



የግሎባል ኤስኤምኢ ፋይናንስ የዕውቅና አቀባበል ስነ ሥርዓት

አዋሽ ባንክ ቀደም ሲል የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በሀገር ደረጃ ስጋት በሆነበት ወቅት ከማስተር ካርድ ፋውንዴሽን፣ ከሥራ ፈጠራ ኮሚሽን እና ፈርስት ኮንሰልት ጋር በመተባበር ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ማገገሚያና ማቋቋሚያ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደረገ ሲሆን ከዚህ አኳያ ባንኩ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት እንዳይዘጉና ሠራተኞቻቸው እንዳይቀነሱ እንዲሁም ፈጠራ የታከለባቸውን የስራ እድሎች መፍጠር እንዲችሉ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከተ እና በዚህም ፕሮግራም ቀደም ሲል የብድር አገልግሎት ማግኘት ያልቻሉ ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የብድር ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም አዋሽ ባንክ ለጥቃቅን አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በሰጠው ብድር ለበርካታ ዜጎች የስራ ዕድል ከመፍጠሩም ባሻገር የብድር አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ ባንኩ ከዘጠኝ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ጋር የብድር ስምምነት ውል መግባቱ ይታወሳል፡፡ በዚሁ መሠረት በተቋማቱ በኩል በርካታ የጥቃቅን አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የብድር አገልግሎት እንዲሁም ቁጥራቸው ቀላል ለማይባል ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር ችሏል፡፡

አዋሽ ባንክ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ቢዝነስ አንቀሳቃሾች ባንኩ የፋይናንስ አገልግሎት መስጠት መጀመሩ አገልግሎቱ ሁሉን አካታችና ተደራሽ እየሆነ መምጣቱን የሚያሳይና ይበል የሚያሰኝ ተግባር ሲሆን ከዚህ አኳያ ባንኩ የስራ ፈጠራ ክህሎት ያላቸው ስራ ፈጣሪዎችን ማበረታታትን ታሳቢ ያደረገና ታታሪዎቹ/ ቀጠሌወን የተሰኘ ፕሮጀክት ቀርፆ ተግባራዊ በማድረግ በርካታ ዜጎችን ተጠቃሚ አድርጓል፡፡

# አዋሽ ባንክ አዲስ የፋይናንስ ቴክኖሎጂ ይፋ አደረገ



“ሳኮስ ኮርፖሬት ቢዝነስ ሶልዩሽን” ቴክኖሎጂ ይፋ ማድረጊያ ስነ ሥርዓት

አዋሽ ባንክ ከአምሪፍ ኸልዝ ጋር በመተባበር በብድርና ቁጠባ ዘርፍ የበለፀገ አዲስ የፋይናንስ ቴክኖሎጂን ነሐሴ 16/2015 ዓ.ም በስካይ ላይት ሆቴል ይፋ አድርጓል፡፡

“ሳኮስ ኮርፖሬት ቢዝነስ ሶልዩሽን” የተሰኘው ቴክኖሎጂ አነስተኛ እና መሰረታዊ የባንክ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ቴክኖሎጂው የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበራትን አገልግሎት ቀልጣፋ ለማድረግ፣ ተደራሽነታቸውን ለማጎልበት፣ ብሎም በዘርፉ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው የአዋሽ ባንክ ሲኒየር ቺፍ ሪቴይል ኤንድ ኤስ.ኤም.ኢ ባንኪንግ ኦፊሰር አቶ ሄኖክ ተሰማ በስነ ሥርዓቱ ላይ ገልጸዋል፡፡

ባንኩ ያስተዋወቀው የፋይናንስ ቴክኖሎጂ ለከፍታ የተቀናጀ የወጣቶች ፕሮጀክት የብድርና ቁጠባው ዘርፍ በነፃ ያቀረበ ሲሆን በዚህ አዲስ ቴክኖሎጂ የአባላት ምዝገባና አያያዝ፣ የብድር አገልግሎት አስተዳደር፣ አክሲዮን እና የአክሲዮን ድርሻ ክፍያን ጨምሮ ሌሎች በርካታ አገልግሎቶች ይሰጣል ተብሏል።

የቁጠባና ብድር ህ/ስ/ማህበራት ለፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነት ዕውን መሆን ከፍተኛ ሚና ያላቸው ቢሆንም አሰራራቸውን ቀልጣፋና ዘመናዊ ለማድረግ የተለያዩ ተግዳሮቶች ይገጥማቸዋል። ለአብነት ለመጥቀስ ያክል በቴክኖሎጂ ያልተደገፈ የአባላት ምዝገባና አያያዝ፣ የሀብት አስተዳደር፣ የቁጠባ ሂሳብ አከፋፈትና አስተዳደር፣ የብድር አፈቃቀድ፣ አሰጣጥና አሰባሰብ ሁኔታዎች በዋነኝነት ተጠቃሽ ናቸው፡፡



“ሳኮስ ኮርፖሬት ቢዝነስ ሶልዩሽን” ቴክኖሎጂ ይፋ ማድረጊያ ስነ ሥርዓት




“ሳኮስ ኮርፖሬት ቢዝነስ ሶልዩሽን” ቴክኖሎጂ ይፋ ማድረጊያ ስነ ሥርዓት

ይህንን በመረዳት አዋሽ ባንክ ላለፉት 29 ዓመታት ያካበተውን ልምድ በመጠቀም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበራትን አገልግሎት ቀልጣፋ ለማድረግ፣ ተደራሽነታቸውን ለማጎልበት፣ ብሎም በዘርፉ ተወዳዳሪ እንዲሆኑና የተቋቋሙበትን አላማ ማሳካት እንዲችሉ ለማድረግ ከአምሪፍ ሄልዝ አፍሪካ ጋር በመተባበር ሳኮስ ኮርፖሬት ቢዝነስ ሶሊዩሽን (SACCOs Corporate Business Solution) የተሰኘ በዓይነቱ አዲስ የሆነ ሚኒ ኮር ባንኪንግ (Mini Core Banking) አበልፅጎ ያለ ምንም ክፍያ ለአገልግሎት አብቅቷል፡፡

ይህ እጅግ ዘመናዊ የሆነ ሲስተም ከሚሰጣችው ዋና ዋና አገልግሎቶች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡ SACCOs Corpo- rate Business Solution የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበራት በውስጥ የአሰራር ደንባቸው መሰረት ለሚገባቸው ሰራተኞቻቸው ብቻ ስም እና የይለፍ ቃል (User name and Password) በመስጠት ሲስተሙን የሚጠቀሙ ሲሆን ይህ ሲስተም መረጃዎች ደህንነታቸው እና ሚስጥራዊነታቸው በተጠበቀ መልኩ የሚመለከታቸው አካላት ብቻ እንዲገለገሉበት ያስችላል፡፡ የተፈቀደላቸው የማህበሩ ሰራተኞች ወደ ሲስተሙ ሲገቡ ዳሽ ቦርድ (Dashboard) ላይ ከሚያገኟቸው መረጃዎች መካከል ጥቅል የአባላቶች ብዛት፣ በሞባይላቸው እና በሲስተሙ የተመዘገቡትን የአባላቶች ብዛት፣ የብድር መጠን፣ አጠቃላይ የተቀማጭ ገንዘብ መጠን እንዲሁም በግራፍ የተደገፉና ለውሳኔ የሚረዱ የማህበሩን ጤናማነት በየጊዜው ለመከታተል የሚያግዙ በርካታ መረጃዎችን ያገኙበታል፡፡

የማህበሩ አባላትም Feature Phone የሚጠቀሙ ከሆነ በUSSD ወይም Smart Phone የሚጠቀሙ ከሆነ በሞባይል መተግበሪያ (Mobile App.) አማካኝነት የቆጠቡትን ገንዘብ መጠን ማወቅ፣ የብድር ጥያቄ ማቅረብና ክፍያ መፈፀም፣ ቀሪ ዕዳቸውን ማወቅ፣ የአክሲዮን ድርሻ መጠንና እንዲሁም ሌሎች መረጃዎችን በቀላሉ ማግኘት የሚያስችል ነው፡፡

# አዋሽ ባንክ የስራ እድል ፈጠራን የሚያበረታታ የ 'ታታሪዎቹ'/ ቀጠሌዋን የሁለተኛ ዙር ፕሮጀክት ይፋ አደረገ




ሁለተኛው ዙር የስራ ፈጠራ ውድድር ማስጀመሪያ ስነ ሥርዓት

አዋሽ ባንክ ማህበራዊ ኃላፊነቱን ከመወጣት አኳያ ስራ ፈጣሪዎችንና ወጣት ትውልድን ለማበረታታትና ተገቢውን የፋይናንስ ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችለውን ሁለተኛ ዙር ፕሮጀክት ቀርጾ ወደ ትግበራ መግባቱን መስከረም 24 ቀን 2016 ዓ.ም ይፋ አድርጓል፡፡

በባንኩ ዋና መ/ቤት በተካሄደው ሁለተኛው ዙር የስራ ፈጠራ ውድድር ማስጀመሪያ ሥነ ሥርዓት ላይ የባንኩ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ፀሀይ ሽፈራው እንደገለፁት የሁለተኛው ዙር መርሃ ግብር ዓላማ ፲ኛው ዙር ሁሉ አዳዲስ የስራ ፈጠራ ባለቤቶችን ለማበረታታት ሁለተኛው ዙር ፕሮጀክት በባንኩ ተቀርፆ የስራ ፈጠራ ውድድር ፕሮጀክትም በተመሳሳይ ስያሜ 'ታታሪዎቹ' በሚል ስያሜ እንዲቀጥል መደረጉን አብስረዋል፡፡ ውድድሩም አዳዲስ የስራ ፈጠራ ክህሎት ኖሯቸው በፋይናንስ እጥረት ምክንያት ተግባራዊ ማድረግ ያልቻሉ በርካታ ስራ ፈጣሪዎችን እንደሚያነሳሳ ገልፀዋል፡፡

'ታታሪዎቹ'/ ቀጠሌዋን የስራ ፈጠራ ውድድር መርሀ ግብር በዋነኛነት ሦስት የስራ ፈጣሪዎችን ተግዳሮቶች ለመፍታት ያለመ ነው፤ ይህም የክህሎት፣ የስራ መነሻ ካፒታልና የዘላቂ ብድር አቅርቦት ችግሮችን ለመቅረፍ ታሳቢ ተደርጎ የተዘጋጀ ነው። የዚህ ዕድል ተጠቃሚ ስራ ፈጣሪዎችም ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች ሥራ ፈላጊዎች ሥራ እንዲፈጥሩ እና ለሀገራቸው የሚተርፉ ብቁ ዜጎችን ለማፍራት መሆኑ ተገልጸዋል።

ፕሮጀክቱን ተግባራዊ የሚያደርግበት የብር አንድ ሚሊዮን የገንዘብ ሽልማትና ቢዝነሱን የሚያስቀጥልበት እስከ ብር አምስት ሚሊዮን ከዋስትና ውጪ የብድር አገልግሎት (Clean Loan) የሚመቻችለት ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በውድድሩ ከሁለተኛ እስከ አምስተኛ የሚወጡት ተወዳዳሪዎችም ጠቀም ያለ የገንዘብ ሽልማትና የቢዝነስ ሃሣባቸውን ተግባራዊ የሚያደርጉበት ከዋስትና ውጪ የብድር አገልግሎት (Clean Loan) የሚመቻችላቸው ይሆናል፡፡

በዚህ የስራ ፈጠራ ውድድር ላይ አዳዲስ እና ችግር ፈቺ የሆኑ የስራ ሀሳቦች ያላቸው ሁሉም የአገራችን ዜጎች የሚሳተፉበት ሲሆን፣ የሥራ ፈጠራ ሃሳባቸውንም፣ በእንግሊዝኛ፣ በአማርኛ፣




ሁለተኛው ዙር የስራ ፈጠራ ውድድር ማስጀመሪያ ስነ ሥርዓት

ወይንም በአፋን ኦሮሞ ማቅረብ ይችላሉ፡፡ የፈጠራ ሃሣባቸውንም የማመልከቻ ቅጽ ከአዋሽ ባንክ ድህረ-ገፅ፣ ፌስ ቡክ እና የቴሌግራም ገጾች እንዲሁም በአካል በመገኘት በሁሉም የባንኩ ቅርንጫፎች ላይ ማግኘት ይችላሉ፡፡ ለአዋሽ ባንክ የሥራ ፈጠራ ውድድር ከሚያመለክቱት ውስጥ ዝቅተኛውን መስፈርት የሚያሟሉ እጩ ተወዳዳሪዎች በሁሉም ክልሎች በተመረጡ የሥልጠና ማዕከላት እንዲሁም በአዲስ አበባና በድሬደዋ ከተሞች የክህሎት ስልጠና እንዲወስዱ እንደሚደረግም ተገልጿል፡፡

በመጀመሪያው ዙር የሚሳተፉት ሁሉም አንድ ሺህ ሰልጣኞች የሙያ ክህሎት ሥልጠና ከየማዕከላቱ ከተሰጣቸው በኋላ የሥራ ፈጠራ ሃሣባቸውን በደንብ አሻሽለው እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡ ተሻሽሎ በቀረበው ሃሣብ መሠረት ተወዳዳሪዎች ተገምግመው በውጤታቸው ደረጃ መሠረት መቶ ሰልጣኞች ወደ ቀጣዩ ዙር የሚያልፉ ይሆናል፡፡ ሌሎች የተቀሩት ተወዳዳሪዎች ሰርተፍኬትና መጠነኛ የኪስ ገንዘብ ይሰጣቸዋል፡፡ ወደ ቀጣዩ ዙር ያለፉት 100 ተወዳዳሪዎች ተጨማሪ ሥልጠናዎች ተሰጥቷቸው የሥራ ፈጠራ ሃሣባቸውን አሻሽለው እንዲያቀርቡ ከተደረገ በኋላ የፕሮጀክት ሃሣባቸው ለዚሁ ሥራ በተመረጡ ዳኞች (Jurry) እንዲገመገም ይደረጋል፡፡ በዳኞች ውሣኔ መሠረት ምርጥ አስር ተወዳዳሪዎች ለቀጣዩ ዙር የሚያልፉ ሲሆን፣ የተቀሩት ደግሞ መጠነኛ ገንዘብና ሰርተፍኬት ይሰጣቸዋል፡፡ በተመሣሣይ መልኩ ለቀጣዩ ዙር ካለፉት አስር ምርጥ ተወዳዳሪዎች ውስጥ የተሻለ የፕሮጀክት ሃሣብ የሚያቀርቡ አምስት ተወዳዳሪዎች ለቀጣይ የመጨረሻው ዙር ውድድር ሲያልፉ፣ የተቀሩት አምስቱ ደግሞ ጠቀም ያለ የገንዘብ ድጋፍና ሰርተፍኬት ይሰጣቸዋል፡፡

ለመጨረሻው ዙር በሚያልፉት አምስት ተወዳዳሪዎች መካከል ከፍተኛ ውድድር እንደሚደረግ የሚጠበቅ ሲሆን፣ የውድድሩ ዳኞችም ከ1ኛ እስከ 5ኛ የሚወጡትን ተወዳዳሪዎች በጥንቃቄ እንዲመረጡ ይደረጋል፡፡ በዚሁ መሠረት በውድድሩ አንደኛ የወጣ ተወዳዳሪ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ የሚያደርግበት የብር አንድ ሚሊዮን የገንዘብ ሽልማትና ቢዝነሱን የሚያስቀጥልበት እስከ ብር አምስት ሚሊዮን ከዋስትና ውጪ የብድር አገልግሎት (Clean Loan) የሚመቻችለት ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በውድድሩ ከሁለተኛ እስከ አምስተኛ የሚወጡት ተወዳዳሪዎችም ጠቀም ያለ የገንዘብ ሽልማትና የቢዝነስ ሃሣባቸውን ተግባራዊ የሚያደርጉበት ከዋስትና ውጪ የብድር አገልግሎት (Clean Loan) የሚመቻችላቸው ይሆናል፡፡

ስራ ፈጣሪ የሆኑ ዜጎቻችን በተለይም ወጣት ወንዶችና ሴት እህቶቻችን የእድሉ ተጠቃሚ በመሆን የቢዝነስ ሀሳባቸውን ዕውን በማድረግ በአገራቸው ዕድገት ላይ የራሳቸውን አሻራ እንዲያሳርፉ የባንኩ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ፀሀይ ሽፈራው ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።

# ባንኩ ማህበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት በተለያዩ ስፍራዎች ትምህርት ቤት እና የህክምና መስጫ ማዕከል አስገነባ




የመማሪያ ክፍሎች የርክክብ እና የምረቃ ስነ ሥርዓት

አዋሽ ባንክ ማህበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት ሰላም ለሀገራችን የልማት ማህበር ከተሰኘ ሀገር በቀል ድርጅት ጋር በመተባበር እና የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግ በደቡብ ወሎ በወረባቦ ወረዳ አተሩ ጎራ ት/ቤት ግቢ ውስጥ ያስገነባውን ዘመናዊ የመማርያ ክፍሎች ለማህበረሰቡ አስረክቧል።

ባንኩ ከምስረታው ጀምሮ የፋይናንስ አገልግሎቱን ተደራሽ ከማድረጉም ባሻገር የማህበረሰቡን ችግር በመረዳት እገዛና ድጋፍ በማድረግ ላይ ሲሆን በቀጣይም በሚደረጉ በጎ ተግባሮች ላይ ከመንግስት ጎን በመቆም ጉልህ ድርሻ እንደሚጫወት የአዋሽ ባንክ ደሴ ቀጠና ዳይሬክተር አቶ ኤልያስ እሸቱ ገልፀዋል፡፡

በተመሳሳይ አዋሽ ባንክ ከአልቢር ዴቨሎፕመንት ጋር በመተባበር በቀቤና ልዩ ወረዳ በፍቃዶ ቀበሌ በሚገኘው የአልቢር ሀሰን ኡንጀ ጤና ጣብያ የተገነባው የእናቶች እና ህፃናት የህክምና መስጫ ማዕከል ተጠናቆ ለምረቃ በቅቷል ።

ባንኩ ከመደበኛው ስራ ጎን ለጎን የማህበረሰቡን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የማህበረሰቡን ችግር በመረዳት ዘርፈ ብዙ እገዛና ድጋፍ በማድረግ ላይ ይገኛል።




የህክምና መስጫ ማዕከል የርክክብ ስነ ሥርዓት

ታታሪዎቹ

# TATARIWOCHU

Empowering The Visionaries

QAXALEEWWAN

Empowering The Visionaries

2nd ROUND

## የማመልከቻ ጊዜ

### ታታሪዎቹ/ቀጠሌዋን

የሁለተኛ ዙር የአዋሽ ባንክ የስራ ፈጠራ ውድድር ለመሳተፍ የማመልከቻ ጊዜ ከጥቅምት 12 እስከ ህዳር 13 ቀን 2016 ዓ.ም መሆኑን እናሳውቃለን!

APPLY NOW

https://tatariwochu.awashbank.com

አዋሽ ባንክ

AwashBank

Nurturing Like the River

8980

www.awashbank.com

# ቆይታ

## “ለአዋሽ ሁልግዜም ጥሩ ነገር እመኛለሁ። ምክንያቱም አዋሽን የማየው ከልጆቼ ውስጥ እንደ አንዱ ነው”

ህይወት አጋጣሚ ናት ሰውን በፈለገው ጎዳና ላትወስድ ትችላለች፣ የወደዱትን ላትሰጥህም ትችላለች፣ ባላሰቡት ጊዜና ሰዓት ልክ እንደ ደራሽ ውሃ በፈለገችው ጎዳና ይዛ እብስ ትላለች። በቃ! ህይወት ብርቱ ሠልፍ ናት ይባል የለ ... መቼም ልጅ ሆነን ወደፊት ትልቅ ሰው ስንሆን ምን መሆን ትፈልጋለህ/ለሽ ስንባል ምኞታችን ብዙ ነው ግን እራሳቸውን ፈልገው የሚያገኙ ምኞታቸው ተሳክቶ እንደተመኘኋት አገኘኋት ብለው የሚዘምሩ ጥቂቶች ናቸው፡፡

ሰው የተመኘውን እና ያለመውን ቢኖር ኖሮ ምነኛ በታደለ ነበር፡፡ በህይወት መንገድ ላይ እራሳቸውን ፈልገው የሚያገኙ ጥቂቶች ናቸው። የተቀሩት ህልምና ምኞታቸውን እንዲሁም መሆን የሚፈልጉትን እንደናፈቁ ያላሰቡትን ሙያ በመስራት ይጠመዳሉ፡፡ ዕጣ ፈንታ ነው። የታደሉት ደግሞ የልጅነት ምኞታቸውን አግኝተው በወደዱት የሙያ ዘርፍ ስኬታማ ሆነው አንቱ ተብለው ለሌሎች መልካም አርዓያ ይሆናሉ፡፡

ውድ የዜና መጽሔታችን ተከታታዮች እኛም በቆይታ አምዳችን የአንድ ስኬታማ እና ታላቅ ሰው የህይወት ገጾች እና የስኬት መንገዶች ልናጋራችሁ ወደድን...

ተወልደው ያደጉት በገጠሩ የሀገራችን ክፍል በምትገኝ አነስተኛ ከተማ ነው፡፡ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ አፈር ፈጭተው ጭቃ አቡክተው ነው ያደጉት፡፡ የተወሰነ የልጅነት ጊዜያቸውን ከወላጆቻቸው ጋር የትውልድ ስፍራቸው በሆነችው አቢደንጎሮ ነው ያሳለፉት፡፡ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በ1988 ዓ.ም በኢኮኖሚክስ ያገኙ ሲሆን በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከኦፊሰርነት እስከ ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅነት በሙያቸው አገልግለዋል።



የሁለተኛ ዲግሪያቸውን ከግሪንዊች ዩኒቨርሲቲ በዓለም አቀፍ ቢዝነስ ሰርተዋል። አቶ ፀሃይ ሽፈራው የአዋሽ ባንክ ዋና ስራ አስፈፃሚ ሲሆኑ ከ2016 ጀምሮ አዋሽ ባንክ በኢትዮጵያ በሁሉም ዋና ዋና መለኪያዎች ቀዳሚ የግል ንግድ ባንክ እንዲሆን ጉልህ ሚና ተጫውተዋል። በዚህም ባንኩ ላስመዘገበው የላቀ አፈጻጸም እና የአቶ ፀሃይ ሽፈራው ከፍተኛ አመራር ግሎባል ፋይናንስ በ2021 ከ50 የአፍሪካ ባንክ ዋና ስራ አስፈፃሚዎች መካከል ዕውቅና በመስጠት ሬፑቲሽናል ፖል ኢንተርናሽናል ሊደርሺፕ አማካሪ አድርጎ ሰይሟቸዋል። የህይወት ተሞክሯቸውን የተመለከቱ አያሌ ጉዳዮች ለተነሳላቸው ጥያቄዎች እርሳቸውም በዕውቀትና በካበተ ልምድ የታገዘ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

አቶ ፀሀይ ከፋና ኤፍ ኤም 120 ደቂቃ ፕሮግራም ከጋዜጠኛ ሳራ መኮንን ጋር ያደረጉትን ቆይታ እኛ ለጽሑፍ እንዲመች አድርገን

## እንደዚህ አቅርበነዋል:- እነሆ ዝለቁ!..

**ፋና ኤፍኤም፡-** ውድ ጊዜዎትን ሰውተው ከእኛ ጋር ቆይታ ለማድረግ ፈቃደኛ ስለሆኑ ከልብ እናመሰግናለን!

**አቶ ፀሀይ፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ!

**ፋና ኤፍኤም፡-** ከትውልድዎና እድገትዎ ብንጀምር ልጅነት እንዴት አለፈ የሚለውን ብናነሳ?

**አቶ ፀሀይ፡-** የተወለድኩት በቀድሞ በወለጋ ክፍለ ሀገር በሆሮ ጉዱሩ ወረዳ ልዩ ስሙ አቢደንጎሮ በሚባል ቦታ ነው። አባቴ አቶ ሽፈራው ኢንሰርሙ፤ እናቴ ወ/ሮ ፉንታዬ አብዲሳ ትባላለች፡፡ ለቤቱ አምስተኛ እና የመጨረሻ ልጅ ስሆን ከእኔ በፊት የነበሩት ወንድሞቼ የተማሩ ናቸው። አባቴ ለየት ባለ መልኩ በትምህርት የሚያምኑ አባት ነው የነበሩት። ለትምህርት ትልቅ ዋጋ ይሰጣሉ። በአካባቢው ላይ ትምህርት ቤት እንዲሰራ ከፍተኛ ዋጋ የከፈሉ ናቸው። በዚህ ምክንያት ልጆቻቸው እንዲማሩ ይፈልጋሉ፡፡ እኔ ደግሞ ወንድሞቼን ከፊት አይቼ እንደነሱ ለመሆን እነሱን እያየው ነው ያደግኩት፡፡ ስለዚህ በእኔ ህይወት ውስጥ አንዱ ትልቅ ዋጋ ያለው አባቴ ነው፡፡ አባቴ ልጅ ሆኜ ደብተሬን ያያል አማርኛ ያነባል እንግሊዝኛ አያነብም። ትምህርት ቤት ውዬ ስመጣ ደብተርህን አምጣ ይልና ደብተሬን ያያል እንግሊዝኛ አያነብም እንግሊዝኛ ደብተር ላይ ኤክስ ካየ ግን ይማታል። በዚያ ምክንያት ክፍል ውስጥ ኤክስ ካገኘው አለቅስ ነበር። ምክንያቱም ማታ ስገባ ስለምመታ ማለት ነው። በዚያ ደረጃ በትምህርት የሚያምኑ የአካባቢውም ሰው እንዲማር የሚፈልጉ አባት ነው የነበረኝ፡፡ እናቴም ብትሆን በጣም ኅበዝ እናት ነበረች፡፡ እና ከእንደዚህ ዓይነት ቤተሰብ ነው የተወለድኩት፡፡

ኢጋጣሚ ሆኖ ድሮ ቤተሰቦቼ የባለባት ቤተሰብ የሚባሉ ናቸው። በኋላ የደርግ መንግስት ሲመጣ ሁሉን ነገር እንደገና ወደ ኋላ መለሰ፤ መሬት፣ የቡና እርሻ ተወሰደባቸው፣ ትርፍ ቤት ተወረሰ። እንደገና አባቴ እኛን ለማስተዳደር ወደ ኋላ ተመልሶ ወደ እርሻ እና ሌሎች ስራዎች ገባ፡፡ እኔ ደግሞ ኢጋጣሚ ከዚያ በኋላ ስለሆነ የተወለድኩት አባቴ ሲሰራ አብሬው እሰራ ነበር። በወቅቱ ከወንድሞቼ ውስጥ በጣም የምሰራው እኔ ነበርኩ። ግን አባታችን ለትምህርት በጣም ትኩረት ስለሚሰጥ ወደ ሌሎች ስራዎች እንድናዘነብል አይፈልግም፤ ወደ ትምህርት ይገፋፋን ነበር፡፡ እንዲህ እንዲህ እያለ አንደኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ እዛው ተማርኩ፡፡ ከዚያ በኋላ ትልቁ ወንድሜ አቶ አወቀ ሽፈራው ይባላል፡፡ እሱ ከሁላችንም ቀድሞ ካደግንበት ከተማ የወጣ ስለሆነ እኛን ማሳደግ ላይ ከአባታችን ቀጥሎ ትልቁን ሚና የተጫወተው እሱ ነበር፡፡

በተለይ ለእኔ እንደ አርዓያ የማየው ስለሆነ ወደ አዲስ አበባ መጣሁ፤ አዲስ አበባ ከመጣሁ በኋላ እሱም እኔን በመቅረጽ ላይ ከፍተኛ ሚና ነበረው፡፡ ከዚያ በኋላ በ1985ዓ.ም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገባሁ፡፡ በ1988 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስድስት ኪሎ በኢኮኖሚክስ የመጀመሪያ ዲግሪዬን ወሰድኩ፡፡ ከመመረቄ በፊት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መጥቶ ከ2.5 በላይ ውጤት ያላቸውን ተመራቂ ተማሪዎች መልምሎ ፈተና ፈተነ፡፡ ከተመረጡት ተፈታኞች ወደ 34 ከሚሆኑ ውስጥ አንዱ ነበርኩ፡፡ ስለዚህ እኔን ማሳደግ ላይ እዚህ ደረጃም እንድደረስ አንዱ ንግድ ባንክ ሚና ነበረው ማለት እችላለሁ ፡፡ የባንክ ኢንደስትሪው እንዲያድግ የንግድ ባንክ ድርሻ ትልቅ ነበር ብዙዎቻችን ከዚያ የወጣን ነን ከዚያ በኋላ ንግድ ባንክ ለዘጠኝ ዓመታት ካገለገልኩ በኋላ አዋሽ ባንክን ተቀላቀልኩ፡፡ አዋሽ ባንክ አስራ ስምንት ዓመት ሰራሁ፤ ከአስራ ስምንቱ አስራ ሦስቱን ዓመት በዋና ስራ አስፈጻሚነት ወይም በፕሬዚዳንትነት ሰራሁ አሁን ይኸው አዋሽ አለው ማለት ነው፡፡



**ፋና ኤፍኤም፡-** ወንድምዎት አቶ አወቀ አዲስ አበባ መጥተው ጤና ሚኒስቴር ውስጥ ነው የገቡት እና ብዙ ጊዜ ታላላቆቻችን የሆኑትን መሆን እንፈልጋለን እና እርስዎ እንዴት ወደ ጤናው አልተሳቡም? እንዴት ወደ ባንኩ ሊሳቡ ቻሉ?

**አቶ ፀሀይ፡-** በጣም የሚገርም ነው! ወንድሜ አወቀን እንደ ሞዴል ስለማየው አንድ ጊዜ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ሆኜ ክረምት ላይ ከክፍለ ሀገር ወደ አዲስ አበባ መጣሁ፡፡ እሱ የሚኖረው ፒያሳ ጊዮርጊስ አካባቢ ነውና እሱ ቤት ነው የምቀመጠው፤ ሁል ግዜ ወደ ማታ ፒያሳ ወክ እደርጋለን እና አንድ ቀን እሱ ከስራ ወጥቶ ሲመጣ ወክ ስናደርግ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በመስኮት በኩል ሰዎች ይሰራሉ፤ ወንድሜ እንደዚህ አለኝ ይሄ ባንክ ነው ባንክ መስራት

## “አዋሽ ባንክ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ ባንክ እንዲሆን እና ከኢትዮጵያ አልፎ በሌሎች አገሮች አገልግሎት እንዲሰጥ እፈልጋለው”

ጥሩ ነው፤ ሙያው በጣም የተከበረ ነው፣ ጥሩ ደመወዝ የሚከፍል ነው፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ባንክ መስራት ማለት መታደል ነው፡፡ ስለዚህ ወደፊት ስትማር ባንክ መስራት አለብህ አለኝ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ባንከር ለመሆን ስሜቱ ውስጤ የገባው በዚያን ግዜ ነው። አጋጣሚ ሆኖ ከዩኒቨርሲቲ ተመርቄ ስወጣም የዕድል ጉዳይ ሆኖ ንግድ ባንክ ገባው፡፡ የሚገርመው የምኖረው ወንድሜ ጋ ስለሆነ ንግድ ባንክ በየአካባቢያችሁ ተመደቡ ሲባል ለመጀመሪያ ጊዜ እሱ ያሳየኝ ቅርንጫፍ ውስጥ ሠራተኛ ሆኜ ተመደብኩ፡፡ ከዚያ በኃላ አራዳ ጊዮርጊስ ንግድ ባንክ ነው ስሰራ የነበረው፤ ቀጥሎም ወደ ዋናው መስሪያ ቤት ተዘዋወርኩ፤ እንግዲህ ከዚያም አልፎ ንግድ ባንክ ውስጥ ከኦፊሰርነት እስከ ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅነት ሰራሁ፡፡ ለተወሰነ ጊዜ ነቀምቴ ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ ነበርኩኝ፤ ከዚያ በኃላ አዋሽ ገባው ማለት ነው፡፡

**ፋና ኤፍኤም፡-** መቼም በልጅነታችን መምህር መሆን፣ ሀኪም መሆን አውሮፕላን አብራሪ መሆን ብለን እንመኛለን እና እርስዎ የልጅነት ህልምዎ ምን መሆን ነበር?

**አቶ ፀሀይ፡-** ድሮ ሀገር ቤት እያለሁ እውነት ለመናገር እንደዚህ ፓይለት እሆናለው ብሎ የገጠር ልጅ አያስብም፤ እኔ በልጅነቴ አስተማሪ ወይም ወታደር መሆን እፈልጋለሁ ብዬ እመኝ ነበር፤ ሁለቱን ነው በጣም የማደንቀው ምክንያቱም አካባቢዬ ላይ የማየው በብዛት አስተማሪና ወታደር በመሆኑ፡፡ ወደ አዲስ አበባ ስመጣ በተለይ ወንድሜ ጋ ቁጭ ብዬ ብዙ መጽሐፎችን አነባለሁ በተለይ አማርኛ ልበወለዶችን፤ ድሮ ላይብረሪ ብዙ የለም፤ ማዘጋጃ ቤት ፣ ወመዘክር እና ብሪቲሽ ካውንስል ብቻ ነበር ላይብረሪ የነበረው፤ ታዲያ በዚያን ግዜ መዘጋጃ ቤት ስለነበረ ላይብረሪ ለመግባት ሰዉ ሌሊት 11፡00 ሰዓት ላይ ሰልፍ ይይዝ ነበረ፡፡ እና ወደ ዩኒቨርሲቲ ለመግባት እንደዛ አንብቤያለሁ፤ ስለዚህ ብዙ ነገሮችን ስላነበብኩ እኔ የትኛውም ሙያ ውስጥ ብገባ የምሰራ ነው የሚመስለኝ፤ የጋዜጠኝነት ሙያንም በጣም ነው የማደንቀው፤ ድሮ ልጅ ሆኜ እነ ወጋየሁ ንጋቱ ትረካ

ሲተርኩ በጣም ነበር የምመሰጠው፤ አባቴ ሬዲዮ ያዳምጣል እና እኔም ሬድዮ አዳምጣለሁ፡፡ እንደ አሁን የሶሻል ሚዲያ ዘመን ሳይሆን ድሮ በሬዲዮ ብዙ ትምህርታዊ ነገሮች ይተላለፋሉ እና ሙያውን በጣም ነው የማደንቀው፤ እንግዲህ አሁን ባንከር ሆኛለሁ፡፡

**ፋና ኤፍኤም፡-** የወላጆችዎን ስሜት ደግሞ እስኪ እንወቅ፤ ልጁ እንዲማር የሚፈልግ አባት ልጁ ተምሮ መጨረሻ ላይ ስራ ይዞ የተሻለ ደረጃ ሲደርስ ለማየት ነውና ምኞታቸው ወላጆችዎ ምን አሉ?

**አቶ ፀሀይ፡-** እኔ ለደረስኩበት ደረጃ አሁን በህይወት የሉም እስከነበሩበት ጊዜ በጣም ከሚፈለገው በላይ ደስተኛ ነበሩ፡፡ የማስታውሰው ከስድስት ኪሎ ስመረቅ አባቴ በጣም አለቀሰ፤ ለሚማር ሰው እራሱን ለሚለውጥ ልዩ ቦታ የሚሰጥ አባት ነው የነበረው፡፡ ጠንካራ አባት ነው፤ መሸነፍ የማይቀበል አባት ነው፤ በተወሰነ መልኩ የእሱ ማንነት ውስጣችን አለ፡፡ እኔም ጋ አለ ብዬ አስባለሁ፡፡ እኔ መሸነፍን አልፈልግም፤ በተፈጥሮዬ የምናገረው ፊትለፊት ነው፡፡ አሁንም የአስተዳደር ዘዴዬ ላይ የአባቴ ሚና አለበት ብዬ ነው የማምነው፡፡

**ፋና ኤፍኤም፡-** ግን ፀሀይ ለምን ተባሉ? ጠይቀው ያውቃሉ?

**አቶ ፀሀይ፡-** ስሜ አንዳንዴ ለሰዎች ለየት ያለ ይሆናል ምክንያቱም ፀሀይ የሴትም ስም ስለሆነ፤ የሚገርመው ቀይ ስለሆንኩኝ ስወለድ በጣም ነጭ ነበርኩ፡፡ በነገራችን ላይ የእናቴን እናት ትመስላለህ ነበር የምባለው፤ እሳቸው በጣም ነጭ ነበሩ ከዚያ መጥተው አልጋ ላይ ሲያዩኝ አይ ይሄማ ፀሀይን ነው የሚመስለው የሚል ጉዳይ ኮሜንት ተደረገ፡፡ ከዚያ በኋላ ፀሀይ ይባል ተብሎ ሌላ ሰው የአባቴ ጓደኛ ናቸው ስም ያወጡልኝ፡፡ በዚያው ፀሀይ ተባልኩ ማለት ነው፡፡ እኔም ስሜን እወደዋለሁ ምክንያቱም ፀሀይ የሁሉ ነገር ምንጭ ስለሆነች፤ የሚገርመው ነገር የሆነ ነገር ላይ ፀሀይ ሽፈራው ብዬ ጽፌ ሰው ሴት ይመስለውና በሴት ከጠሩኝ በኋላ ክፍል ውስጥ እኔ አቤት ብዬ ስነሳ ሲደነግጡ አያለሁኝ፤ ምክንያቱም ፀሀይ የሚለው ስለሚጠበቅ አንዳንዶች ደግሞ ወደፀሀይ ይሉኛል፤ ወንድ ሊያደርጉኝ ግን ትክክለኛው ስሜ ፀሀይ ነው፡፡

**ፋና ኤፍኤም፡-** ተማሩ፣ ስራ ያዙ፣ አሁን ያሉበት ደረጃ ላይ ደረሱ በዚህ መሀል ደግሞ የእርስዎን ህይወት መስርተዋል፤ ስለ ቤተሰብዎ እናውራ? እንተዋወቃቸው?

**አቶ ፀሀይ፡-** እሺ ባለቤቴ ወ/ሮ ቆንጂት ሐይሌ ነው የምትባለው፤ ሦስት ልጆች ወልደናል፤ የመጀመሪያ ልጄ ሴት ነች፤ ሁለቱ ወንዶች ናቸው፡፡ የመጀመሪያዋ ልጄ በዚህ ዓመት አስራ ዘጠኝ ዓመቷ ነው ዩኒቨርሲቲ ገብታለች፡፡ አሜሪካን ሀገር ድሬክሰር ዩኒቨርሲቲ ነው የገባችው፡፡ በጣም ጎበዝ ልጅ ነች፡፡ ሴቶች ላይ በጣም ነው የማምነው እና ብዙ ሴት ልጅ ቢኖረኝ ደስ ይለኛል፡፡ ለምን ሴቶች ከዚህ በላይ መሄድ አለባቸው ብዬ አምናለሁ፡፡ ሁለቱ ልጆቼ እዚሁ ከእኛ ጋር ናቸው፤ እየተማሩ ነው ያሉት፡፡ ብዙውን ጊዜ ከቤተሰቤ ጋር ነው የማሳልፈውና የቤተሰብ ሰው ነኝ፡፡ በተቻለ መጠን ስራዬን ቢሮ ማሸነፍ እፈልጋለሁ ወደ ቤቴ ስገባ የቢሮ ስራ ይዤ መግባት አልፈልግም። ቢሮ መናደድ አለ፣ ከሰው ጋር መጋጨት አለ እሱን ይዤ ወደ ቤቴ ላለመግባት ከፍተኛ ጥረት ነው የማደርገው፡፡ ከልጆቼ ጋር ያለኝ ግንኙነት በጣም ጥብቅ ነው፡፡ ለልጆቼ ቅርብ ነኝ፤ እንታገላለን፣ ቴኒስ እንጫወታለን፣ ማታ ማታ ሁልጊዜ ወክ እናደርጋለን፤ እግዚአብሔር ይመስገን! በቤተሰቦቼ በጣም ነው የምኮራው እግዚአብሔርንም አመሰግነዋለሁ ጥሩ ቤተሰብ ስለሰጠኝ፡፡

**ፋና ኤፍኤም፡**- እስኪ ከባለቤትዎ ወ/ሮ ቆንጂት ጋር የተዋወቁበትን ሁኔታ እናስታውስ እንዴት ተጀመረ ፍቅሩ?

**አቶ ፀሀይ፡-** እግዚአብሔር ረድቶኝ ቶሎ ነው ያገባሁት ብዬ ነው የማስበው፤ ሳገባ ገና ንግድ ባንክ ኦፊሰር ሆኜ ነው ያገባሁት፡፡ከባለቤቴ ጋር ከተጋባን አሁን ወደ ሃያ ዓመት ሆነን፤ ቶሎ በማግባቴ ዕድለኛ ነኝ! ይኸው አሁን ትላልቅ ልጆች ኖረኝ፡፡ መጀመሪያ ከባለቤቴ ጋር የተዋወቅነው በአንድ ዘመዴ በኩል ነው፡፡ አቶ ስለሺ ቦረና ይባላል፤ አሁን አሜሪካን ሀገር ነው የሚኖረው፤ ወ/ሮ ቆንጂት ኤንጂኦ ውስጥ ይሰራሉ፤ አንድ የአይሪሽ ኤንጂኦ ከእሳቸው ጋር ዘመዴ አንድ ሴሚናር ላይ ይገናኛል፤ ከዚያ በኋላ ንግድ ባንክ እየሰራው አንድ ጥሩ ልጅ እዛ አይቻት ተዋወቅን ስለዚህ እሷን ማግባት አለብህ አለኝ፤ እኔ በዚያን ግዜ ለማግባት ሀሳብ የለኝም፡፡ አንተ አይደለህም ሚስት የምትመርጥልኝ እኔ ነኝ የምመርጠው አልኩት፤ ከዚያ አይ አይሆንም አለ፤ አጋጣሚ ሆኖ የእሷም ቤተሰቦች እኛ አካባቢ ናቸው፡፡ አባቷ አቶ ሀይሌ ጪብሳ ይባላሉ፤ ድሮ የወሊጋ የደቡብ እርሻ ስራ አስኪያጅ የነበሩ በጣም የተማሩ እና የታወቁ ናቸው፡፡ ከዚያ በኋላ እንደቀልድ አስተዋወቀን፤ እውነትም ወ/ሮ ቆንጂትን ሳያቸው ወደድኳቸው፡፡ ተሰካና ብዙም አልቆየንም ቀጥታ ወደ ትዳር አመራን፡፡ እግዚአብሔር በሰው ህይወት ውስጥ አንድ ሰው ምክንያት ያዘጋጃል እና እግዚአብሔር ነው ከኋላ ያለው ነው ብዬ ነው የማምነው፡፡

**ፋና ኤፍኤም፡-** እንደው አቶ ፀሀይ ባለቤትዎ ወ/ሮ ቆንጂትን ገና የመጀመሪያ ቀን እንዳዩዋቸው ነው የወደዱዋቸው?

**አቶ ፀሀይ፡-** ተገናኘን ምሳ አብሮ ጋበዘን ቦሌ ሩዋንዳ ወሎ ሰፈር አካባቢ ድሮ ካራማራ ሬስቶራንት ነበረ አሁን ፈርሶ ቦታው ላይ ህንፃ እየተሰራበት ነው፡፡ እዛ ምሳ በላን፤ በደንብ አየኋት አጋጣሚ ቤተሰብ ውስጥ ሀዘን ስለነበረ ሀዘን ልብስ ለብሳለች፤ ከዚያ በኋላ በቀጣይም ተገናኘን፡፡ የሚገርመው ነገር ባገኘኋት ቁጥር ብዙ ነገሮቿን ወድድኩ ማለት ነው፡፡ ከዚያ ይበልጥ እየተቀራረብን ሄድን፤ ጊዜ ሳናጠፋ ወደ ቁም ነገር ቶሎ ብለን ገባን፡፡ በተፈጥሮዬ ከመልክ በላይ የውስጥ ጥሩነት ይማርከኛል። በራሷ የነበራት በራስ መተማመን፣ ለነገሮች ያላት አመለካከቶች እኔ ከማውቀው ለየት አለብኝ፤ አንድ በጣም የማስታውሰው የመጀመሪያ ዕለት ዘመዴ ካገናኘን በኋላ ተገናኘን እና ሁለተኛው ቀን ምሳ ልጋብዝሽ አልኳት፤ በሁለተኛው ቀን ቀድማ ደውላ ምሳ ልጋብዝህ አለችኝ እና ከፈለች፡፡ በወቅቱ በጣም ነው የተገረምኩት ምክንያቱም በዚያን ወቅት ከሴቶች ጋር ስንገናኝ ወንዱ ነው ከፋዩ የሚሆነው እና ከዚያ በኋላ አንድ ቀን እሷ ስትጋብዝ አንድ ቀን እኔ ስጋብዝ ለተወሰነ ሲቀጥል አስተዳደጓ፣ የማይባት በራስ መተማመኗ ልዩ ሆነብኝ፤ እሷ የከተማ ልጅ ስለሆነች ባህሪዋ እኔ ከመጣሁበት አካባቢ ለየት ይላል በዚያ ምክንያት ውስጧን ነው በጣም የወደድኳት፤

**ፋና ኤፍኤም፡-** በዛንግዜ በምን ነበር ስልክ የምትደዋወሉት?

**አቶ ፀሀይ፡-** በዚያን ግዜ ሞባይል ስልክ የለም፡፡ በቀጥታ ስልክ ነበር የምንደዋወለው እና የቤቷን ስልክ ጭምር በቃሌ ነበር የማውቀውና እደውላለሁ፤ በወቅቱ እናት አባት ይፈራል፤ ስልክ ደግሞ ስንደውል ከሱቅ ነበር የምንደውለው፤ ስለዚህ ማታ ማታ ወንድሜ እንዳያየኝ ተደብቄ ወጣ እልና ሱቅ ላይ ስልክ እደውላለሁ፤ እንደዚህ እያደረግን ነበር የጓደኝነት ጊዜያችንን ያሳለፍነው፡፡ ስለዚህ እኔ በሞባይል ዘመን የጠበስኩ አይደለሁም፡፡

**ፋና ኤፍኤም፡-** ከስራ ውጭ ባለው ጊዜ ቤት ውስጥ ከልጆችዎ ጋር ስፖርት መስራትና ጨዋታ አለ ከዚያ ባለፈ ግን ለልጆችዎ ወደ ኩሽና ገባ ብለው ምግብ አብስለው ያውቃሉ?

**አቶ ፀሀይ፡-** በእውነቱ በዛ ጠንካራ አይደለሁም፡፡ ትልቋ ልጄ ስጋና የእንስሳት ተዋፅኦ ነገሮችን አትበላም፤ ሁለተኛውም ልጄ በእሷ ተጽዕኖ መሰለኝ ስጋ ነገር ብዙ አይወድም፡፡ እና አሁን እነሱ ለራሳቸው መስራት ጀመረዋል፡፡ ምክንያቱም እራሳቸውን እንዲችሉ ነው የምንፈልገው፤ አልጋቸውን ያነጥፋሉ፣ የራሳቸው የሆኑ ስራዎችን ነገም ተግዳሮት ስለሚያጋጥማቸው ሰራተኛም ቢኖር ቤት ውስጥ ባለቤቴም እንዲሰሩ ነው የምትገፋፋቸው፡፡ በዚያ በዚያ ምክንያት ከእነርሱ ጋር መሆን ነው እንጂ ያን ያህል ምግብ ማዘጋጀት ላይ ጎበዝ አይደለሁም፡፡

**ፋና ኤፍኤም፡-** እንደው ግን ቢሰራና ቢመጣልኝ ደስ ይለኛል የሚሉት የምግብ ዓይነት ምንድነው?

**አቶ ፀሀይ፡-** ከምግቦች ሽሮ በጣም ወዳለሁ፡፡ከዚያ ውጭ ብዙም አይደለሁም ለስጋ ያለኝ ፍላጎት ኖርማል ነው፡፡ እንግዲህ አሁን ደግሞ ያው ክብደት ለመቀነስ ብዙም አይበላም፡፡ ትንሽ ትንሽ ነው የምበላው ግን ከምግቦች ሽሮን እመርጣለሁ፡፡

**ፋና ኤፍኤም፡-** ባየውና ባሳካው የሚሉት ነገር ምንድነው?

**አቶ ፀሀይ፡-** እንደ አዋሽ ስራ አስፈጻሚነቴ ለአዋሽ ባይና አይቼ ከዚያ በኋላ እኔ ብጨርስም ብዬ የማስባቸው የመጀመሪያ አዋሽ ባንክ አሁን ያለበት ህንጻ ያሰሩት የቀድሞ ዋና ስራ አስፈጻሚ ወይም ፕሬዚደንት የነበሩት አቶ ለይኩን ብርሃኑ ናቸው፡፡ አቶ ለይኩን ብርሃኑ በዚህ በባንክ ኢንዱስትሪ ውስጥ በጣም የታወቁ ናቸው እሳቸው ይህንን ህንጻ ሰርተው ለአዋሽ አስረክበዋል፡፡ አሁን አዳዲስ ባንኮች እየመጡ ነው ትላልቅ ህንጻዎችን እየገነቡ ነው፡፡ አሁን እኛ ሜክሲኮ አካባቢ ቦታ ሊሰጠን ነው፡፡ ለአዋሽ ባንክ አንዱ የማስበው ነገር አዋሽን የሚመጥን አንድ ትልቅ ዋና መስሪያ ቤት ልስራ ብዬ አስባለሁ፡፡ ሁለተኛው ለ2030 ያስቀመጥነው ራዕይ ከሀገርም አለፈን የማሰብ ነገር ነው፡፡ አሁን የውጭ ባንኮች የሚገቡ ከሆነ ውድድሩ ቀላል አይሆንም፡፡ አዋሽ ባንክ ከውጭ ባንክ ጋርም በተጓዳኝ የሚሰራበትን ሁኔታዎች ለማመቻቸት አስባለሁ፡፡ ከዚያ በኋላ "አዋሽ ባንክ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ ባንክ እንዲሆን እና ከኢትዮጵያ አልፎ በሌሎች አገሮች አገልግሎት እንዲሰጥ እፈልጋለሁ" እና እሱም ቢሳካ በጣም ደስ ይለኛል፡፡

**ፋና ኤፍኤም፡-** በህይወት ውጣውረድ ብዙ እንማራለን እና የተፈተኑበት ጊዜ ነበረ?

**አቶ ፀሀይ፡-** አዋሽን የሚያክል ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ ሆኖ መስራት ቀላል አይደለም፡፡ ከዚህ በፊት የተለያዩ ጉዳዮች አጋጥመውኛል፡፡ ለምሳሌ፡ በአንድ ወቅት ጂም ሰርቼ ስወጣ ባለፈው ስርዓት ላይ ነው፤ የምነዳው መኪና በድንጋይ ተመታ መሀል አስገብተው ከዚያ ታሰርኩ፤ ለምንድነው? ሲባል ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ ሰው ገጭተህ ገድለሃል ተብዬ የታሰርኩበት ጊዜ ነበረ፡፡ ነገር ግን እኔ በዚያ ሰዓት ጂም ውስጥ እንደነበርኩ ብዙ የሚመሰክሩ ሰዎች ነበሩ፤ ያንን መስማት አልተፈለገም፡፡ ወደ አስራ አምስት ቀን ማዕከላዊ ታሰርኩ፡፡ በኋላ ለምንድነው ያ ነገር ሊከሰት የቻለው ብዬ ሳስብ ባንኩ አካባቢና ከባንኩም ጀርባ ምንድነው ያለው የሚለውን ነገር ማጣራት እንፈልጋለን ተባለ፤ የዚያን ግዜ ያሰሩኝ ባለስልጣኖች ከዚያም ባሻገር ከዚህ ወደ ውጭ ሄጄ እንድቀር ብዙ ግፊቶች ነበሩ፡፡ አንድ ግዜ ቤተሰቤን ይዤ አሜሪካን ሀገር ሄጄ ጋዜጣ ላይ የአዋሽ ባንክ

ፕሬዚዳንት ቤተሰባቸውን ይዘው ፈረጠጡ ተብሎ ተጻፈ ውጭ ሄጂ እንድቀር፤ ሁልጊዜ ብዙ ተግዳሮቶች ይኖራሉ፡፡ ምክንያቱም ባንክ ብዙ ፍላጎት ያለበት፣ የብዙ ሰዎች ፍላጎት ያለበት ፍላጎቱን ለማሳከት የሚሄድበት ቦታ ነውና በየቀኑ ብዙ ነገሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ የእኔ ዋና ዓላማ ግን አዋሽና አዋሽ ነው፡፡ በማኔጅመንት መርሄ በአዋሽ ላይ አልደራደርም። እግዚአብሔር ረድቶኝ ባንኩ በእኔ ዘመን በጣም አድጓል፡፡ እኔ ስቀበል ስልሳ አንድ ቅርንጫፍ ነበረ አሁን ግን ከስምንት መቶ ሰባ በላይ ቅርንጫፎች አሉ። አዋሽን ስቀበል ተቀማጭ ገንዘብ እታች ነበር ያለው፤ አሁን በብዙ ቢሊዮን ሆኗል፡፡ አዋሽ ባንክን እኔ ስቀበል ከግል ባንኮች መሪ አልነበረም፤ ሁለተኛ ነበር ሦስተኛና አራተኛ የነበሩትም ደርሰውበት ነበር፤ አሁን በሁሉም ነገር የሚመራ ባንክ ነው፡፡ እንግዲህ አስራ ሦስት ዓመት በዋና ስራ አስፈጻሚነት መስራት ቀላል አይደለም፤ ብዙ ፈተናዎች ውስጥ አልፌ ነው እዚህ የደረስኩት፡፡ የነገውን እግዚአብሔር ያውቃል “ለአዋሽ ግን ሁልግዜም ጥሩ ነገር እመኛለሁ፡፡ ምክንያቱም አዋሽን የማየው ከልጆቼ ውስጥ እንደ አንዱ ነው” እንደ አራተኛው ልጄ ነው የማየው፡፡

**ፋና ኤፍኤም፡-** አዋሽ ባንክ እንግዲህ ለተከታታይ ሁለት ዓመታት በግሎባል ፋይናንስ አፍሪካ ውስጥ ካሉ ባንኮች ቀዳሚ ሆኖ ተመርጧል፤ እርስዎ ደግሞ ስመ ጥር የባንክ ፕሬዚዳንት በመባልም ዕውቅና አግኝተዋልና እንኳን ደስ አላችሁ እላለሁ!

**አቶ ፀሀይ፡-** በጣም አመሰግናለሁ!

**ፋና ኤፍኤም፡-** ተሸላሚ መሆን ስሜቱ እንዴት ነው? እንግዲህ እርስዎ እየመሩት ስለሆነ አዋሽ ተሸላሚ የሆነው እንደው ስሜትዎን ብንጋራ...

**አቶ ፀሀይ፡-** እንደ አንድ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደተፈጠረ ካምፓኒ በተለይም ደግሞ ላለፉት ሃያ ስምንት፣ ሃያ ዘጠኝ ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ እንደሰራ ተቋም በአፍሪካ ደረጃ ዕውቅና ማግኘት በጣም ትልቅ ነገር ነው፡፡ ግሎባል ፋይናንስ ዋና መስሪያ ቤቱን ኒዮርክ ያደረገ የየአህጉሮችን ምርጥ ባንኮች የሚመርጥና የሚሸልም ተቋም ነው፡፡ በዚህ ምርጫ ላይ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ምርጫውን በመጠቀም የሚሳተፉ ብዙ አማካሪዎች ይሳተፉበታል፡፡ ስለዚህ ላለፉት ሁለት ዓመታት የኢትዮጵያ ምርጥ ባንክ ተብሎ አዋሽ ባንክ ተመርጧል፡፡ በእውነቱ እኔ ደግሞ የዚህ ባንክ መሪ ሆኜ እዚህ ቦታ ተገኝቼ ይህ ባንክ በዚህ ደረጃ መመረጡ ከፍተኛ ኩራት ነው የሚሰማኝ፤ ለሀገሬም ኩራት ነው ብዬ አስባለሁ፤ ሌሎችም ባንኮች ልክ እንደ አዋሽ ባንክ የተሻለ ስራ እንዲሰሩ የሚያበረታታቸው ይመስለኛል፡፡

ከዚህ ባለፈ የአፍሪካ ምርጥ ሃምሳ ዋና ስራ አስፈጻሚ ተብሎ ባንክ ላይ ምርጫ ተደርጓል፡፡ ከዚያ ውስጥ ደግሞ አንዱ ሆኜ እኔ ይህንን ባንክ ስለምመራ ተመርጫለሁ፡፡ በአፍሪካ ደረጃ ወደ ስምንት፣ ዘጠኝ መቶ ባንኮች አሉ፤ ከዛ ውስጥ ሃምሳ ምርጥ ዋና ስራ አስፈጻሚ ተብሎ መመረጥ ቀላል አይደለም፡፡ እዚህ ላይ በመድረሳችን ደስ ብሎኛል፤ ወደፊት የተሻለ ስራ ለመስራት የሚያበረታታን ይመስለኛል። ባለፉት አስርት ዓመታት አዋሽ ባንክ ኢትዮጵያ ውስጥ በፍጥነት እያደጉ ካሉ ተቋማት ግምባር ቀደም ነው፡፡ በየሁለት ዓመቱ እራሱን ደብል ያደርጋል አሁን ደግሞ ጊዜው በጣም የተግዳሮት ግዜ ነው፤ መንግስትም የውጭ ባንኮች እንዲገቡ እየፈቀደ ነው ያለው፤ ድሮ የባንክ ስራ የማይሰሩ የቴሌኮሚዩኒኬሽንና የቴክኖሎጂ ካምፓኒዎች የባንክ ስራ እንዲሰሩ ተፈቅዶላቸዋል፡፡ ከዚያም አልፎ ደግሞ ካፒታል ማርኬት እየተቋቋመ ነው፡፡ አሁን ደግሞ በዚህ ዓመት በአዲስ መልክ ማኬንዚ ካምፓኒ የተባለ በዓለም ላይ ስትራቴጂ በመስራት ታዋቂ የሆነ አምጥተን አሁን የአምስት ዓመት ስትራቴጂ ሰርተናል፡፡ ስለዚህ በሚቀጥሉትም ዓመታት አዋሽ ባንክ የተሻለ ውጤት ያስመዘግባል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

**ፋና ኤፍኤም፡-** በድጋሜ እንኳን ደስ ያላችሁ ብያለሁ!

**አቶ ፀሀይ፡-** አመሠግናለሁ።

**ፋና ኤፍኤም፡-** አቶ ፀሀይን ምን ያዝናናቸዋል?

**አቶ ፀሀይ፡-** ብዙ ግዜ እኔ ያው ስራ ላይ ነው የማሳልፈው፡፡ ከእስፖርት ሁለት ነገር እወዳለሁ፡፡ የመጀመሪያው እንደ ሁሉም ኢትዮጵያዊያን እግር ኳስ እወዳለሁ፡፡ እግር ኳስ ጊዜ ካለኝ ቤቴ ተከፍቶ ካለ ነው የማይው ድንገት ተከፍቶ ማለት ነው፡፡ ድሮ ከሀገር ውስጥ የተመዘገበ የቡና ደጋፊ ነበርኩ፡፡ ከውጭ ደግሞ የሊቨርፑል ደጋፊ ነኝ፡፡ ድሮ ልጅ ሆኜ የመጀመሪያ እዚህ ቶታል ኢትዮጵያ እግር ኳስ ሲያሳይ አዲሳባ ስመጣ ጥቁር ቴሌቪዥን ነው ያየሁት፡፡ የዚያን ግዜ ልጅ ሆኜ ሊቨርፑል ገናና ነበረ ፡፡ ከዚያን ግዜ ጀምሮ ወደድኩት፡፡ በዚህ ምክንያት የሊቨርፑልን ጨዋታዎች ባይ ደስ ይለኛል፡፡ ከዚያ ውጭ ቴኒስ ማየት እወዳለሁ፡፡ አሁን ጆኮቪችን በጣም አደንቀዋለሁ፡፡ ቴኒስና እግር ኳስ ሳይ በጣም እዝናናለሁ፡፡ ከዚያ ውጭ እንደ ቤተሰብ ብዙ ግዜዬን የማሳልፈው ከቤተሰብ ጋር ነው፡፡

**ፋና ኤፍኤም፡-** ግዜዎትን ስለሰጡን እንመሰግናለን፡፡

**አቶ ፀሀይ፡-** እኔም እንግዳ አድርጋችሁ ስለጋበዛችሁኝ በጣም አመሰግናለሁ፡፡


ሀቅዎን በሀቂቃ!
አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like The River
ikhlas
Nurturing Like the River
8980
www.awashbank.com

# ምልከታ
# ዘመቻ ዲጅታል!!!

## ሃሎ ስራ አስኪያጆች...
## ይሰማል?

ጊዜው የውድድር ነው፤ በውድድሩ ትራክ ውስጥ ደግሞ ብርቱ ፉክክር አለ፤ ታዲያ በዚህ ውድድር መሪነታችንን እና አሸናፊነታችንን አስጠብቀን ለማስቀጠል ሁላችንም በተሰጠን የስራ ኃላፊነት ያለንን ክህሎትና ዕውቀት በመጠቀም የላቀ ውጤት በማስመዝገብ የነደፍነውን ዕቅድ ከግብ ለማድረስ እና የባንካችንን የ2030 ስትራቴጅክ ዕቅድ ለማሳካት በትጋት መስራት ይጠበቅብናል፡፡



የሀብት ማሰባሰብ ዘመቻ

ነገሩ እንዲህ ነው ምስራቅ አዲስ አበባ ቀጠና ጽ/ቤት በዓል በአካባቢያቸው ካቀረበላቸው በርካታ ዕድሎች መካከል አንዱን ለመጠቀም በማሰብ ባለፉት  የበዓል ገበያ በከተማችን ትልቁ በሆነው በአቃቂ የቁም ከብት ገበያ ሀብትን የማሰባሰብ ዘመቻ አካሂደዋል። ከረፋድ 4:30 ጀምሮ እስከ ገበያው ማብቂያ ከሰዓት 7:30 ድረስ በአካባቢው ላይ ያሉ ስምንት ቅርጫፎች በዚህም ዘመቻ ተሳትፎ አድርገዋል፡፡

በዕለቱ ሰፊ ካሬ በሚሸፍነው በዚህ የቁም ከብት ለበዓል በሚሸመትበት በአቃቂ ገበያ በተደረገው ዘመቻ በቅርንጫፎች ያለውን የበዓል የደንበኞች አገልግሎት በማይጎዳ  መልኩ ከመደበኛው ስራ ጋር በማጣጣም በተደረገው መርኃ ግብር የባንኩን የዲጂታል ክፍያ ስርዓቶች (በተለይ አዋሽ ብር) በስፋት ማስተዋወቅ ተችሏል፡፡

በአዋሽ  ብር መገበያየት ከስርቆት  ከሀሰተኛ ብር  ኖት እና ከመሳሰሉት ጥፋቶች እንደሚከላከል  በተጨማሪም  ጊዜና ጉልበትም እንደሚቀንስ ለዕለቱ ገቢያተኞች ስለ አዋሽ ብር የግንዛቤ ማስጨበጫ የተሰጠ ሲሆን በውጤቱም ከደንበኞች ትልቅ ተቀባይነት በማግኘት የካርድ እና የአዋሽ ብር አዳዲስ ደንበኞችን በዘመቻው በተሳተፉ ቅርንጫፎች በዕለቱ መመልመል ተችሏል፡፡

በብር የተገበያዩ የቅርንጫፎቹ ደንበኛ የሆኑ የቁም ከብት ሻጮች በአቅራቢያው ባሉ ቅርንጫፎች ብር እንዲያስገቡ ምክረ  ሀሳብ በማቅረብ  ውጤት  ተገኝቶበታል። በተጨማሪም 105 ስንቅ ያላቸው አዳዲስ አካውንቶች የሶስት  ሰዓት  እድሜ በነበረው ዘመቻ ተከፍተዋል።

በአጠቃላይ ዘመቻው ባንካችን በሕብረተሰባችን ምን ያህል ተወዳጅ እንደሆነ በድጋሚ በይበልጥ ማረጋገጥ የተቻለበት እንደ ነበር ከቀጠና ጽ/ቤቱ የተገኘው መረጃ ያስረዳል፡፡

በዘመቻው በመሳተፍ ይህንን መልካም አርዓያ ለፈጸሙ የባንካችን የምስራቅ አዲስ አበባ ቀጠና ጽ/ቤት የቅርንጫፍ ስራ አስኪያጆች እና ሰራተኞች ላሳዩት ትጋት ምስጋና ይገባቸዋል።

ጉዞው ይቀጥላል...

ሁላችንም ይህንን የምስራቅ አዲስ አበባ ቀጠና ጽ/ቤት ዘመቻ ዲጂታል እንቀላቀል!



የሀብት ማሰባሰብ ዘመቻ

MUDAY




# እኛ ጋር ይቆጥቡ!

## አብረውን ይደጉ!

8980

www.awashbank.com

አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like The River

# በውድቀት የተገኘ የስኬት ታሪክ

ሕይወት ምናልባት በውድቀት ውስጥ የስኬት ትልቁ ምሳሌ ነው ማለት ይቻላል። ማ ዩን ይባላል የቢዝነስ ገበያ ቦታን ጨምሮ በርካታ የቻይና ታዋቂ ድረ-ገጾችን ያቀፈው ታታሪው ሥራ ፈጣሪ ወጣት ነው። ማ ዩን (ጃክ ማ) የተወለደው እ.ኤ.አ. መስከረም 10/1964 በቻይና ሃንግዙ ዢጂያንግ ግዛት ሲሆን በድሃ ቤተሰብ ውስጥ ያደገው በባህል አብዮት ጊዜ ነው።

ወጣቱ ገና በልጅነቱ ቱሪስቶች ያረፉባቸውን ሆቴሎች ይጎበኝ ስለነበር ከብዙዎቹ ጋር የመገናኘት ዕድሉን አግኝተዋል። እንዲያውም ጃክ ማ ስሙን ‘ጃክ’ ያገኘው ከቱሪስቶቹ አንዱን በመገናኘት እንደሆነ ይነገራል። ዛሬ ማ በዓለም ካሉት እጅግ ሀብታም ሰዎች አንዱ የሆነበት ምስጢር ምን ይሆን? ታሪኩ ባጭሩ እነሆ?




## ቀደምት ወድቀቶች

ማ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን ሁለት ጊዜ፣ መካከለኛ ደረጃ ትምህርቱን ሦስት ጊዜ፣ የዩኒቨርስቲ መግቢያ ፈተናውንም ሶስት ጊዜ ወድቋል። በፖሊስ ኃይል እንዲሁም በKFC (Kentucky Fried Chicken) ምግብ ቤት ለመቀጠርም ካመለከቱት 24 ሰዎች መካከል ማ ብቻ ነው ውድቅ የነበረው። ለሃርቫርድ አሥር ጊዜ አመልክቶ አንዱም አልተሳካም። በአጠቃላይ ለ30 የተለያዩ ዕድሎች አመልክቶ ሁሉም አልተሳካለትም። በመጨረሻም ከብዙ ልፋት በኋላ በወቅቱ በየወሩ 12 ዶላር የሚያገኘውን የእንግሊዘኛ መምህርነት ሥራ ማግኘት ቻለ።

## በመሳካት ጽናት

ምንም እንኳን እነዚህ ሁሉ ውድቀቶች እና ውጣውረዶች ቢኖሩም ማ በአንዳችም ተስፋ አልቆረጠም። በአላማው ጸንቷል። ታታሪው ማ ችሎታውን በመተማመን ህልሙን ከዳር ለማድረስ ለስራ ፈጠራ ትኩረት በመስጠት የትርጉም አገልግሎት ንግድ በመጀመር ከበይነመረቡ ጋር የተዋወቀበትን ተርጓሚ ሆኖ አሜሪካንን ጎበኘ። ስለ ኮምፒውተሮች ወይም ስለ ኮድ አወጣጥ ምንም አይነት ቴክኒካል እውቀት የሌለው ማ በወቅቱ ለዚህ አዲስ ክስተት ፍላጎት ነበረው።

# ለስኬት የሚደረገው ትግል

ማ እ.ኤ.አ. በ1999 አስራ ሰባት የሚሆኑ ጓደኞቹን ሰብስቦ ለአነስተኛ እና መካከለኛ ንግዶች በበይነመረብ (በኢንተርኔት) ላይ የገበያ ቦታ ሀሳብ አቀረበ። ለዚህም ስራ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ማ ሃሳቡን ለማቅረብ ወደ ሲሊከን ቫሊ በድጋሚ ወደ አሜሪካ ተጓዘ። ነገር ግን ሃሳቡን ውድቅ በማድረግ "የማይጠቅም፣ ዘላቂነት እና ትርፋማ ያልሆነ ስራ ነው" ተብሎ በመተቸቱ የተለመደው መሰናክል ገጠመው። ማ በአቋሙ እና በአላማው በመፅናት ህልሙን እውን ለማድርግ የሚችለውን ሁሉ ለማድረግ ሞከረ። ከዚህ በመነሳት ሥራ ፈጣሪው ጃክ ማ Alibaba.com እና የግብይት ጣቢያውን Taobao.com በመፍጠር ወደ ገበያ ገብተዋል።

ነገር ግን እ.ኤ.አ በ2003 ኩባንያው በመጀመሪያዎቹ ሶስት አመታት ምንም አይነት ገቢ ባለማግኘቱ እና በአስራ ስምንት ወራት ውስጥ ኪሳራ ሲደርስበት ለአሊባባ መጪው ጊዜ አሁንም የጨለመ ሆነበት። በወቅቱ የቻይና ኢኮኖሚ ገና በጅምር ላይ እያለ የንግድ ድርጅቶች እና የመንግስት ባለስልጣናት የበይነመረብ ገበያው ላይ ጥርጣሬ ነበራቸው። ማ ኩባንያው እንዲያድግ እና እንዲሰብ ሌተቀን ቢሰራውም አሊባባ ግን የውስጥ ችግሮችም አጋጥመውታል።


ማ ግን አሊባባን ወደፊት ለማራመድ የነበረውን ክፍተት በመቀየር ቡድኑን አንድ ማድረግ ችሏል። ከዚህ በመነሳት ቀደም ሲል በቻይና በይነመረብ ምርቶቻቸውን በብቸኝነት ሲያቀርቡ የነበሩ እንደ ኢቤይ ያሉ ተቋማት በላይ ውጤታማ መሆን ጀመሩ፣ በአምስት ዓመታት ውስጥም ማ እና አሊባባ በቻይና የበይነመረብ ንግድ ሥራን ከመቆጣጠር ባለፈ ወደ አለም አቀፉ ገበያ ይበልጥ ማስፋፋትና ማደግ ጀመረ።

ከብዙ ውጣውረድ በኃላ በጃክ ማ ሀሳብ አመንጪነት የተመሰረተው ግዙፉ የኢ-ኮሜርስ አሊባባ በዓለም ላይ ትልቅ ታሪክ ሰርቷል። ታታሪው ጃክ ማ አሊባባን ለማሳደግ አዳዲስ የቴክኖሎጂ ግብአቶችን በመጠቀም ወደ ተለያዩ ኢንዱስትሪዎች እና ሎጅስቲክስ በማስፋፋቱ አሁን በፕላኔታችን ላይ ካሉት ታላላቅ የኢ-ኮሜርስ ኩባንያዎች መካከል አንዱ እንዲሆን አድርጎታል።

ከዚህ በመነሳት በዓለም ላይ ካሉት እጅግ ሀብታም ሰዎች እና ትላልቅ ኩባንያዎች መካከል አንዱ እንዲሆን በማድረግ ካፒታሉም ከ43 ቢሊየን ዶላር በላይ እንዲያድግ አድርጓል።

ዛሬ የቻይና የኢንተርኔት ገጽታን የሚያውቁ ሰዎች ጃክ ማ የሚለውን ስም በቀላሉ ይረዱታል። የእሱ አስተዋጽኦ በቻይና ኢኮኖሚ ላይ ብቻ ሳይሆን በኢ-ኮሜርስ ኢንዱስትሪ ላይም ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል።

ምንጭ:https://smartmoney.angelone.in/blog/the-success-story-of-jack-ma-chinese-businessman/



# Photo Reel










Annual Management Meeting










**Green Legacy Seeds Planting Program**

# The LEADING

Private bank
In Ethiopia



አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

8980
www.awashbank.com